# በቤት ውስጥ ንግግርን መለማመድ

እንዴት በጥሩ ሁኔታ የንግግር ልምምድ አድርገሃል/አድርገሻል! ምንም እንኳን በአሁኑ ሰዓት ከንግግር ባለሙያው ጋር ተገናኝቶ መለማመድ ባይቻልም በቤት ውስጥ መለማመድ የሚያስችሉ አዝናኝ ተግባራት መከወኛ እዚህ ድህረ ገጽ ላይ አዘጋጅተናል www.leadersproject.org ታድያ እነዚህ ልምምዶች በሚደረጉብት ወቅት የንግግር ባለሙያ ወይም የቤተሰብ አባል እንዲረዳችሁ መጠየቅን እንዳትረሱ!

## የጨዋታ ሰሌዳዎች:- *የሚከተለውን ለማብራራት የሚረዳ ቪዲዮ እዚህ ይገኛል፡፡*

ዝግጅት፡-

1. “ዛህራ” ባለነጠብጣብ ጠጠር መሰል መጫወቻ ያስፈልጋል (በቤት ውስጥ ዛህራ እንዴት መስራት እንደሚቻል የሚያሳዩ መመሪያዎች እዚህ ይገኛሉ!)፣ በተጨማሪም በሰሌዳው ላይ ለማንሸራሸርም አንድ ማሳያም ያስፈልጋል፡፡ ማሳያውም ድንጋይ፣ሳንቲም ወይም ባቄላ ሊሆን ይችላል፡፡

2. ከምትለማመዱት ድምጽ ጋር የሚሄደውን የሰሌዳ ጨዋታ አግኙ፡፡

   a. በቤት ውስጥ ማተሚያ(printer) ካለ ማተም ይቻላል በኃላም፣ቀለም በመቀባት አሳምሮ መጫወት ይቻላል፡፡

በቤት ውስጥ ማተሚያ ከሌለ ግን፣ ኢንተርኔት ላይ ያለውን ምስል በማየት መሳል ትችላለችሁ፡፡ በተጨማሪም ቀለም በመቀባት ማሳመራችሁን አረጋግጡ፡፡

   b. ይህን ማድረግ ካልተቻለ ቀለም በመቀባት ወይም ስዕል በመሳል ቃላቶቹን መለማመድ ትችላላችሁ፡፡

3. ከቃላቶቹና ከድምጾቹ ጋር በተያያዘ ሊያግዛችሁ የሚገባ “ረዳት “ ፈልጉ ፡፡ ተጫወቱም!

- ዝግጁ በምትሆኑበት ጊዜ ዘሃራውን አንከባሉት/ማንከባለል፡፡ ማሳያውን በሰሌዳው ስታንቀሳቅሱት እያንዳንዱን ድምጽ እየደጋገማችሁ በሉት፡፡ እያንዳንዱን ድምጽ በትክክል ማለት እንድትችሉ ረዳታችሁ ከእናንተ ጋር እየሰራ መሆኑን አረጋግጡ፡፡

- የጨዋታ ሰሌዳውን በሙሉ ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድባችኋል?

## የተረት መጻሕፍት:- *የሚከተለውን ለማብራራት የሚሆን ቪዲዮ [እዚህ] ይገኛል፡፡*

ዝግጅት፡-

1. የትኛው ድምጽ ላይ እየሰራችሁ ነው? እርግጠኛ ካልሆናችሁ የንግግር ሃኪሙን ወይም እንክብካቤ ሰጪውን ጠይቁ ፡፡
2. ከድምጹ ጋር የሚሄደውን ተረት ፈልጉ፡፡
3.
   a. ቤት ማተሚያ ካለችሁ በማተም ቀለም በመቀባት ልታሳምሩትና ከዚያም ልትጫወቱበት ትችላላችሁ፡፡
   b. ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ኢንተርኔት ላይ ያሉትን ምስሎች በማየት እና መጽሐፉን በመመልከት እያንዳንዱን ገጽ ራሳችሁ ለመሳል ሞክሩ፡፡ አንድ አይነት ካልሆነ ችግር የለውም፤ የፈጠራ ችሎታችሁን ተጠቀሙ፣ከዚያም በጣም ጥሩ ይሆናል፡፡ ቀለም መቀባትና ማሳመራችሁንም አረጋግጡ፡፡
   c. ቀለም እየቀባችሁ ወይም እየሳላችሁ በመጽሐፉ ገጾች ላይ ያሉትን ቃላት ተለማመዱ፡፡ተጫወቱም!

1. አዲሱን መጽሐፍ አንድታነቡት እና ድምጾቹን እንድትለማመዱ የሚረዳችሁን / የሚያግዛችሁን "ረዳት" ፈልጉ፡፡
2. እያነበባችሁ መጽሐፉን ለመተወን ሞክሩ ፡፡